# ቤተ-መፃሕፍትና ምሁራዊ ነፃነትን አስመልክቶ የቀረበ መሪ-ሃሳብ

ይህ መሪ-ሃሳብ በቤተ-መፃሕፍት ማህበራትና ተቋማት ዓለም-አቀፍ ፌዴሬሽን ሥር በተቋቋመው «መረጃን የማግኘት ነፃነትና ሃሳብን የመግለጽ ነፃነት ኮሚቴ» ተዘጋጅቶ በፌዴሬሽኑ የሥራ አስፈፃሚ ቦርድ እ.ኤ.አ. ማርች 25/1999 ዘሄግ ከተማ በኔዘርላንድ የፀደቀ ነው፡፡

---

የቤተ-መፃሕፍት ማህበራትና ተቋማት ዓለም-አቀፍ ፌዴሬሽን በተባበሩት መንግሥታት ዓለም-አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ መሠረት ምሁራዊ ነፃነትን ይደግፋል፤ ይጠብቃል፤ ያራምዳል፡፡

ፌዴሬሽኑ የሰው ልጆች ዕውቀትን፣ የፈጠራ እሳቤዎችንና ምሁራዊ እንቅስቃሴዎችን የማግኘትና እንዲሁም አመለካከታቸውን በይፋ የማንፀባረቅ መሠረታዊ መብት ያላቸው መሆኑን በአጽንኦት ይገልፃል፡፡

ፌዴሬሽኑ የማወቅ መብትና ሃሳብን የመግለጽ ነፃነት የአንድ መርህ ሁለት ገጽታዎች መሆናቸውን ያምናል፡፡ ለሃሳብና ለህሊና ነፃነት የማወቅ መብት ቀዳሚ አስፈላጊ ጉዳይ ሲሆን የሃሳብ ነፃነትና ሃሳብን የመግለጽ ነፃነት ደግሞ መረጃን ለማግኘት ነፃነት አስፈላጊ ሁኔታ ነው፡፡

ለምሁራዊ ነፃነት መርህ በጽናት መሥራት ለቤተ-መፃሕፍትና ለመረጃ ሙያ ቀዳሚ ሃላፊነት መሆኑን ፌዴሬሽኑ አበክሮ ይገልፃል፡፡

ቤተ-መፃሕፍትና የቤተ-መፃሕፍት ሠራተኞች ለምሁራዊ ነፃነት፣ ያልተገደበ መረጃን ለማግኘት መብትና ሃሳብን ለመግለጽ ነፃነት መርሆዎች ራሳቸውን ተገዢ እንዲያደርጉና የቤተ-መፃሕፍት ተጠቃሚዎችን ምስጢራዊነት እንዲያከብሩ ፌዴሬሽኑ ጥሪ ያቀርባል፡፡

ፌዴሬሽኑ እነዚህ መርሆዎች ተቀባይነት እንዲያገኙና ተግባራዊ እንዲሆኑ አባላቱ በንቃት እንዲንቀሳቀሱ ያበረታታል፡፡ ይህንኑ መሠረት በማድረግ ፌዴሬሽኑ የሚከተለውን ይገልፃል፡፡

- ቤተ-መፃሕፍት መረጃ፣ የሃሳብ ውጤቶችና የፈጠራ ሥራዎች የሚቀርብባቸው ነፃ መድረኮች ናቸው፡፡ እንዲሁም ቤተ-መፃሕፍት የዕውቀት፣ የሃሳብ ውጤቶችና የመረጃ መረማመጃ መግቢያ በር ሆነው ያገለግላሉ፡፡

- ቤተ-መፃሕፍት ለግለሰቦችና ቡድኖች በዕድሜ ዘመን ለማይቋረጥ ትምህርት፣ በነፃነት ውሳኔ ለመስጠት ችሎታና ለባሕላዊ ዕድገት ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣሉ፡፡
- ቤተ-መፃሕፍት ምሁራዊ ነፃነት እንዲዳብርና በተገቢው እንዲጠበቅ አስተዋጽዖ የሚያደርጉ ሲሆን መሰረታዊ ዲሞክራሲያዊ እሴቶችና አለም አቀፋዊ ሲቪል መብቶች እንዲከበሩ ይረዳሉ፡፡
- የዕውቀት መገለጫና ምሁራዊ ሥራዎች በቀላሉ እንዲገኙ ማረጋገጥና ማመቻቸት የቤተ-መፃሕፍት ድርብ ሃላፊነት ነው፡፡ ይህን ሃላፊነት ከግብ ለማድረስ ቤተ-መፃሕፍቱ የህብረተሰቡን የተለያዩ ክፍሎች ልዩነትና አንድነት የሚያንፀባርቁ በዓይነታቸው በርከት ያሉ ስብስቦችን ማግኘት፣ መጠበቅና ለተጠቃሚዎች ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
- የቤተ-መፃሕፍቱ ስብስቦችና አገልግሎቶች ምርጫና አቅርቦት ከሙያዊ ጠቀሜታቸው አንፃር ብቻ መመራት ይኖርበታል እንጂ በፖለቲካ፣ በሞራል ወይም በሃይማኖታዊ አመለካከቶች አለመወሰኑን ቤተ-መፃሕፍት ማረጋገጥ ይገባቸዋል፡፡
- ቤተ-መፃሕፍት መረጃዎችን በነፃነት ማግኘት፣ ማደራጀትና ማሰራጨት የሚኖርባቸው ሲሆን ማናቸውንም ዓይነት ቅድመ-ምርመራ (ሳንሱር) ሊቃወሙ ይገባሉ፡፡
- ቤተ-መፃሕፍት ማናቸውንም ስብስቦች፣ የመጠቀሚያ መሣሪያዎችና አገልግሎቶች ለሁሉም ተጠቃሚዎች በእኩልነት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ በዘር፣ በእምነት፣ በፆታ፣ በዕድሜ ወይም በሌላ በማናቸውም ምክንያት ልዩነት ሊያደርጉ አይገባም፡፡
- የቤተ-መፃሕፍት ተጠቃሚዎች ማንነታቸውን ያለመግለጽና ግላዊ ምስጢራቸውን ከሌሎች የመጠበቅ መብት አላቸው፡፡ የቤተ-መፃሕፍት ባለሙያዎችና ሌሎች የቤተ-መፃሕፍት ሠራተኞች የተጠቃሚዎችን ማንነት ወይም የሚጠቀሙትን የስብስብ ዓይነት ለሌሎች ሦስተኛ ወገኖች መግለጽ አይኖርባቸውም፡፡
- የገቢ ምንጫቸው የሕዝብ ሃብት የሆነ ቤተ-መፃሕፍትና ለሕዝብ መጠቀሚያነት ክፍት የሆኑ ቤተ-መፃሕፍት የምሁራዊ ነፃነትን መርህ አክብረው መጠበቅ ይኖርባቸዋል፡፡
- የቤተ-መፃሕፍት ባለመያዎችና ሌሎች በቤተ-መፃሕፍት ውስጥ የሚሰሩ ሠራተኞች ይህን የምሁራዊ ነፃነትን መርህ አክብረው የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው፡፡
- የቤተ-መፃሕፍት ባለሙያዎችና ሌሎች በቤተ-መፃሕፍት ውስጥ የሚሰሩ ባለመያዎች በአሰሪዎቻቸውና በተጠቃሚዎች በኩል ያለባቸውን ሃላፊነት ሊወጡ ይገባል፡፡ በእነዚህ ሁለት ሃላፊነቶች መካከል አለመጣጣም ወይም ግጭት በሚኖርበት ጊዜ ለተጠቃሚዎች ያላቸው ሃላፊነት ቀዳሚነት ሊኖረው ይገባል፡፡